**የፕሮጀክት ርዕስ**፡- ከአውሮፓ ለሚመለሱ ኢትዮጵያውያን የሚደረግ ዘላቂ ድጋፍ
**አስፈጻሚ ኤጀንሲ፡-** የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ- የስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት
**የገንዘብ ድጋፍ፡-** የአውሮፓ ህብረት
**የፕሮጀክት ቆይታ ጊዜ፡-** ሶስት ዓመት (ከግንቦት 2018 እስከ ሚያዚያ 2021)

## የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች፡-

1. ከአውሮፓ ህብረት አባል አገራት እንዲሁም ከኖርዌይ እና ከስዊዘርላንድ የተመለሱ ኢትዮጵያውያን ፍልሰተኞች፣
2. የተመረጡ ለስደት ተጋላጭ የማህበረሰብ አካላት፣
3. በተመላሾች ዙሪያ በተለይ በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ብ/ብ/ህ፣ ሶማሌ እና ትግራይ ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚሰሩ የመንግስት ባለድርሻ አከላት፣

## የፕሮጀክቱ ዓላማ፤

1. ከስደት ለሚመለሱ ኢትዮጵያውያን በግለሰብ እንዲሁም በማህበረሰብ ደረጃ ዘላቂ የሆነ ሥነ-ልቦናዊ፤ ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ድጋፍ ማመቻቸት፣
2. የስደትና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ (ስ.ጉ.ኤ) እና ከስደት ተመላሾች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ባለ ድርሻ አካላትን ድርጅታዊ እና ቴክኒካዊ አቅም በማሳደግ በመልሶ ማቋቋም ላይ የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ድጋፍ ማድረግ፣

## የተመላሾች አቀባበል ቅደም ተከተል

### እርከን 1

የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት የስደት ተመላሹን ጉዳይ በተመለከተ ፓስፖርት እና/ወይም ሊሴፓሴ ለሚሰጠው የኢትዮጵያ መንግስት ያስተላልፋሉ፤

### እርከን 2

የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተመላሾችን መረጃ ለስ.ጉ.ኤ የስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ያሳውቃል፤

- ከስደት ተመላሾች ወደ ትውልድ ሀገራቸው ከመመለሳቸው በፊት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለስ.ጉ.ኤ የስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የተመላሾችን ሠነድ ማለትም ፓስፖርት፣ ሊሴፓሴ፣ የኤምባሲውን ማስታወሻ (Note Verbale) እና ሌሎች ተዛማጅ ሠነዶችን በማያያዝ ያቀርባል፤
- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተመላሾቹ የሚነሱበትን እና የበረራ መነሻና መድረሻ መርሐ-ግብር እንዲሁም ልዩ ፍላጎታቸውን በተመለከተ ያለውን መረጃ ለስ.ጉ.ኤ የስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ያሳውቃል።

### እርከን 3

የስ.ጉ.ኤ ከስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በቦሌ ዓለም ዓቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ለተመላሾች አቀባበል ያደርጋል፤

- ተመላሾች አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረሱ የስ.ጉ.ኤ የስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኦፊሰሮች በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በመገኘት ተመላሾችን ይቀበላሉ፤ ልየታ አድርገውም ይመዘግባሉ፤
- በተደረገው የመጀመሪያ የተጋላጭነት ልየታ መሠረት እያንዳንዱ ተመላሽ ከአውሮፕላን ማረፊያ ወደ ጊዜያዊ መጠለያ ወይም ወደ ሆስፒታል/የሕክምና ማዕከል (አስቸኳይ የሕክምና ክትትል የሚያስፈልግ ከሆነ) እንዲጓጓዝ እገዛ ይደረጋል፤

### እርከን 4

በመቀበያ ማዕከል ከደረሱ በኋላ የሚደረግ ድጋፍ፡-

- የህክምና ድጋፍ የማያስፈልጋቸው ተመላሾች በአዲስ አበባ ጊዜያዊ ማረፊያ (ማቆያ) እንዲያርፉ ይደረጋል፤
- ተመላሾች እንደ ምግብ፣ ውሃ፣ ማረፊያ እና የንፅህና መጠበቂያ ቁሳ ቁሶች፣ የጤና ምርመራዎች እንዲሁም የስነ-ልቦና እና የመልሶ መቋቋም የምክር አገልግሎት ከሦስት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ባረፉበት የማቆያ ማዕከል እንዲያገኙ ይደረጋል፤

### እርከን 5

ሁሉም ተመላሾች ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ሲመለሱ የመጓጓዣ እና ጊዜያዊ መጠለያ ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል፤

- ሁሉም ተመላሾች ወደ ትውልድ አገራቸው ለመመለስ የመጓጓዣ እና ጊዜያዊ መጠለያ እንዲያገኙ የገንዘብ ድጋፍ ይደረጋል፤
- የመጨረሻ መዳረሻቸው አዲስ አበባ ለሆኑ ተመላሾች የ60 ዩሮ፣ ከአዲስ አበባ ውጭ በ400 ኪ.ሜ ርቀት ከቤተሰቦቻቸው ለሚቀላቀሉ የ100 ዩሮ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ውጭ ከ400 ኪሎ ሜትር በላይ ለሚጓዙ ደግሞ የ150 ዩሮ ድጋፍ በኢትዮጵያ ብር እንዲያገኙ ይደረጋል፤

### እርከን 6

ተመላሾች በአዲስ አበባ የስነ-ልቦናና የህክምና አገልግሎት ያገኛሉ፤

- ተመላሾች አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ በሚደረገው ልየታ የስነ-ልቦና እርዳታና ድንገተኛ ህክምና የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ወደ ቤተሰቦቻቸው ወይም ወደ ማህበረሰባቸው ከመመለሳቸው በፊት በአዲስ አበባ ለአጭር ጊዜ (ከ6 ወር የማይበልጥ) እርዳታ ያገኛሉ፤
- ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ተመልሰው ከቤተሰቦቻቸው ወይም ከማህበረሰቡ ጋር የመዋሃድ/የመቀላቀል ችግር ላጋጠማቸው ተመላሾች ለአጭር ጊዜ (ከሦስት ወር የማይበልጥ) የቤት ኪራይ ድጋፍ ሊሰጣቸው ይችላል፤ ሆኖም ይህ ድጋፍ የሚሰጠው በስ.ጉ.ኤ ከስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሚያስቀምጠው የብቁነት መስፈርት ከተሟላ ብቻ ነው።

### እርከን 7

በክልል እና በዞን/በወረዳ የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ መስጠት፡-

- ተመላሾች ለአእምሮ ጤንነት ደህንነት፣ በክልል እና በዞን ደረጃዎች ህክምናና የምክር አገልግሎት ድጋፍ ያገኛሉ። ሆኖም እንዲህ ዓይነቱ ድጋፍ ለተደረገላቸው ተመላሾች ተጨማሪ ክትትልና ህክምና የሚፈቀደው በጤና ባለሙያ ውሳኔ መሠረት ይሆናል፤
- ትምህርታቸውን ለመቀጠል / ለመጀመር ፈቃደኛ ለሆኑ ተመላሾች ፕሮጀክቱ በቂ የትምህርት አቅርቦቶችን ይሸፍናል። ሆኖም ይህ ድጋፍ የሚሰጠው በስ.ጉ.ኤ ከስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሚያስቀምጠው የብቁነት መስፈርት ከተሟላ ብቻ ነው፤
- ተመላሾች መሰረታዊ የፋይናንስ ዕውቀት /Financial Literacy/፣ የድርጅት ልማት /Enterprise Development/ እና ሌሎች የአጭር ጊዜ የሙያ ስልጠና ሊሰጣቸው ይችላል፤
- ተመላሾች አስፈላጊውን ስልጠና ከጨረሱ በኋላ በግልም ሆነ በጋራ የራሳቸውን የንግድ ስራ ዕቅድ አዘጋጅተው በማቅረብ ከፕሮጀክቱ እና ከመንግስት ባለድርሻ አካላት በቀጥታ ድጋፍ ያገኛሉ፤
- ፕሮጀክቱ የተዘጋጀውን የንግድ ስራ ዕቅድ ይገመግማል፤ ስራ ለመጀመር የሚያስፈልጉ ዕቃዎችን ይገዛል፤ ያሰራጫል እንዲሁም የንግድ ስራ አመራርና ክትትል ያደርጋል፤
- የግለሰብ የሙያ ክህሎት ማዳበሪያ እና የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ አጠቃላይ ወጪ በአንድ ተመላሽ (ለአዋቂዎች ብቻ) ከ3,000.00 ዩሮ ምንዛሪ እኩል ከሆነ የኢትዮጵያ ብር አይበልጥም። የዕቃዎች ግዢም ሆነ ማንኛውም ክፍያ የሚፈጸመው በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በኩል ብቻ ነው። ስለሆነም ለተመላሾች በምንም ሁኔታ ጥሬ ገንዘብ በእጅ አይሠጥም፤

- ለተመላሾች የንግድ ድርጅት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተመላሹ በመንግስት የተቀመጡ የቁጥጥር ደንቦችን ሁሉ ለማሟላት ተገቢውን የንግድ ፈቃድ እና ለንግድ ስራው የሚጠየቀውን ማንኛዉንም ተጓዳኝ ፈቃዶች ማግኘት ይጠበቅበታል፡፡

## በፕሮጀክቱ የማይሸፈን የመልሶ ማቋቋም እገዛ

- ከተመላሹ የሶሺዮ-ኢኮኖሚያዊ መልሶ ማቋቋም ትግበራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው የግል ዕቃዎች ግዢ፣
- የጥራት እና/ወይም የአቅርቦታቸው ሁኔታ አስተማማኝ ካልሆነ በስተቀር በመንግስት የሚሰጡ አገልግሎቶች (እንደ ሰልጠናና ትምህርት፣ ህክምና፣ አስተዳደራዊና የሕግ አገልግሎቶች)፣
- እንደ ሰርግ ያሉ የግል ዝግጅቶች ወጪዎች እና የእዳ ክፍያ ወይም የገንዘብ መቀጮ እና መሰል ወጪዎች፣

## የመልሶ ማቋቋም እርዳታን ለማግኘት ምን መደረግ አለበት?

- እያንዳንዱ ተመላሽ በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ወይም በፕሮጀክቱ የክልል መልሶ ማቋቋሚያ ማዕከሎች ወይም በዞን/ወረዳ የስራ ፈጠራና ምግብ ዋስትና ቢሮዎች በተቻለ ፍጥነት ቀርቦ ማመልከት አለበት፡፡ ይህ በአውሮፕላን ማረፊያው ውስጥ ያልተገኙ ወይም ራሳቸውን ያላስተዋወቁ ተመላሾችን ያጠቃልላል፡፡ ስለሆነም አገልግሎቱን ለማግኘት የሚቀርቡበት ቦታ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ፣ በፕሮጀክቱ የክልል መልሶ ማቋቋሚያ ማዕከሎች ወይም በዞን/ወረዳ የስራ ፈጠራና ምግብ ዋስትና ቢሮዎች ይሆናል፡፡

- የዞን/ወረዳ የስራ ፈጠራና ምግብ ዋስትና ቢሮዎች ተመላሾች ማመልከታቸውን ለፕሮጀክቱ የክልል መልሶ ማቋቋሚያ ማዕከል ያሳውቃሉ፡፡ የፕሮጀክቱ የክልል ኦፊሰር ተመላሹ ወደሚገኝበት ቦታ በመሄድ ያገኛዋል፡፡

- ተመላሾች የፕሮጀክት ጽ/ቤቱንም ሆነ የክልል መልሶ ማቋቋሚያ ማዕከሎችን በስልክ ወይም በኢሜል ወይም በአካል ማግኘት ይችላሉ፡፡ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ መደበኛ የስራ ሰዓት ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋት 2:30 እስከ ምሽት 11:30 ነው፡፡ ሆኖም ተቀባይ አስተናጋጆችና የሚመለከታቸው የፕሮጀክቱ ሰራተኞች በቦሌ ዓለም ዓቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ተመላሾችን ለመቀበል፣ ለመመዝገብ እና የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ለመስጠት ሳምንቱን ሙሉ ለ24 ሰዓታት ዝግጁ ናቸው፡፡

- እያንዳንዱ ተመላሽ ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጋር በመወያየትና በመመካከር የመልሶ ማቋቋም ዕቅዱን ትግበራ ማጠናቀቅ አለበት፤

- እያንዳንዱ ተመላሽ በተመለሰ በ12 ወራት ውስጥ በፕሮጀክቱ የሚከፈሉ ጠቅላላ ክፍያዎች መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እና ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር መተባበር አለበት፡፡ ሆኖም ተጋላጭ የሆኑ ተመላሾችን ነባራዊ ሁኔታዎች በመገንዘብ የተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ሊለዋወጥ ይችላል፡፡


**የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አድራሻ፡-**

የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ
የስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት
አድራሻ፡-
አዲስ አበባ፣ የካ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 09፣ ጎዳና 9_2425፣ የቤት ቁጥር B42_19፣ ከመገናኛ ወደ “ሳህሊተ ምህረት አደባባይ” በሚወስደው መንገድ ወደ “ዲሚትሪ ሆቴል” በሚወስደው መንገድ ከ “ሶሎቴ ሆቴል” ጎን ነው፡፡

ፖ.ሳ.ቁ. 84
ይድረስ (Attention)፡- ለስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት፣
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስልክ ቁጥሮች፡-
+251-111-872-0366 ወይም +251-111-872-1376
or +251 – 111 – 854 – 8635
ኢሜይል፡- info.rrpmo@arra.et
በቦሌ ዓለም ዓቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የሚቀበልዎት ኦፊሰር፡-
አቶ ረድኤት ብርሃኑ - የተመላሾች አራይቫል ሪሰፕሽኒስት
የሞባይል ስልክ ቁጥር:- +251-911-55-5272
ኢሜይል፡- redietbirhanu1@gmail.com ወይም
rediet.birhanu@arra.et


ለበለጠ መረጃ www.arra.et ይጎብኙ!


Implemented by ARRA

Funded by the European Union


# ለስደት ተመላሾች ስለሚሰጥ ድጋፍ የተዘጋጀ መረጃ




## ዘላቂ የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ




ማሳሰቢያ፡-
ይህ በራሪ ፅሁፍ በአውሮፓ ህብረት የገንዘብ ድጋፍ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይዘቱ የስ.ጉ.ኤ የስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊነት በመሆኑ የአውሮፓ ህብረትን አቋም አያንፀባርቅም፡፡